# Renting in Seattle

# ቤት መልቀቅ

የኪራይ ስምምነትን ስለመጨረስ መታወቅ ያለበት በርካታ ነገ አሉ። ይህ በራሪ ወረቀት መልቀቅ በሚፈልጉበት ጊዜ ወይም የእርስዎ አከራይ እንዲለቁ ማሳሰቢያ በሚሰጥዎ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ያወራል። ለደኅንነት የተቀመጠው ገንዘብ የሚመለስበት፣ አከራይ ማየት ያለበት እና የማስለቀቂ ሂደቱን ይናገራል።

ይህን ድህረ ገጽ ይጎብኙ www.seattle.gov/rentinginseattle ወይም በሚከተለው ላይ በ Renting in Seattle Helpline (ሲያትል ውስጥ ኪራይን ለማገዝ የሚረዳ መስመር) ላይ በ(206) 684-5700 ይደውሉ።



City of Seattle

Amharic

# መልቀቅ በሚፈልጉበት ጊዜ

- ከወር እስከ ወር ተከራይተው ከሆነ፣ ሊለቁ የሚፈልጉበት ወር ከማለቁ በፊት ለእርስዎ አከራይ በጽሑፍ ማሳሰቢያ ቢያንስ ከ20 ቀናት በፊት መስጠት ይጠበቅብዎታል።
- ለተወሰነ ጊዜ ሊዝ ካለዎት፣ ማሳሰቢያውን ምን ማካተት እንዳለበት ለማየት የሊዝ ስምምነቱን ይመልከቱ።
- ተገቢውን ማሳሰቢያ መስጠት አለመቻል በሚከተሉት የኪራይ ጊዜያት ውስጥ ለኪራይ እርስዎ ተጠያቂ ያደርጋል።
- ሊዙን መጣስ በጣም ውስን እና ግልጽ በሆኑ ሁኔታዎች ሥር በሕግ እንዲፈቀድ ያደርጋል። ሊዙ የእርስዎ ቀነ ገደብ ከመድረሱ በፊት የግድ ማቋረጥ ካለብዎ፣ ከእርስዎ አከራይ ጋር ለማቋረጥ በጋር የስምምነት ድርድር ያድርጉ እና አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ሕጋዊ ምክር ያግኙ።






# የእርስዎ አከራይ መቼ እንዲለቁ ይፈልጋል

ሊዝ ካልዎት፣ ሊዙ እንዴት ሊቋረጥ እንደሚችል የሚናገረውን ክፍል ይመልከቱ። በተወሰነ ቀን ውስጥ የሚያልቅ ከሆነ፣ ለማደስም ምንም አማራጭ የማይሰጥ ከሆነ እና ከወር እስከ ወር ወደ መከራየት ስምምነት የማይለወጥ ከሆነ፣ እንደ ሊዙ ስምምነት መሰረት መልቀቂ ሊኖርብዎ ይችላል።

- ከወር እስከ ወር የተከራዩ ከሆነ፣ የእርስዎ አከራይ የእርስዎን ተከራይነትን ለማቋረጥ  የግድ ጉዳይ ሊኖረው ይገባዋል። የጽሑፍ ማሳሰቢያ በግልጽ የመነሻ ምክንያቱን መግለጽ ያለበት ሲሆን እርስዎን ከመኖሪያው ለማስለቀቅ የሚያስገድደውን ማሳሰቢያ ማቅረብ አለበት። በሚከተለው ድኅረገጽ ላይ 18 የሚሆኑ የመነሻ ምክንያቶች አሉ *www.seattle.gov/rentinginseattle*
- አንዳን ፍትሃዊ የሆኑ መነሻ ምክንያቶች የመሬት ባለቤቱን የቦታ መለወጫ ድጋፍን መክፈል እንዳለበት ያስገድደዋል።
- እንዲለቁ የሚያዘውን ማሳሰቢያ ከእርስዎ አከራይ ካገኙ፣ ሁሉንም ሕጋዊ መመዘኛዎችን ያሟላ ተገቢነት ያለው ማሳሰቢያ መሆኑን ለማየት ወደ Renting in Seattle Helpline ይደውሉ።

# የመሊቀቂያ ቅድመ ሁኔታ

- አሳማኝ የሆነ ማልበስ እና መቅደድ ብቻ ተቀንሶበት ቤቱን በተከራይበት ጊዜ በነበረበት ሁኔታ መመለስ እንዳለብዎ ሕግ ያስገድድዎታል።
- የእርስዎ አከራይ ወደ የኪራይ ስምምነት በገቡ ጊዜ ያቀረበልዎትን የማረጋገጫ ዝርዝር ሊያቀርብልዎ የሚገባ ሲሆን ቤቱን አበላሽተው ከሆነ መሰረት ማድረግ ያለብዎ ያንን የማረጋገጫ ዝርዝር ላይ በመንተራስ ነው።
- ብልሽት ካለ፣ የእርስዎ አከራይ ዕድሜን እና የዕቃ ብልሽቱን ሁኔታ ታሳብ ማድረግ ያለበት ሲሆን ከትክክለኛው ዋጋ በተጨማሪ ሊያስከፍልዎት አይችልም።
- ከእርስዎ አከራይ ጋር ከመውጣትዎ በፊት አብረው ሆነው በክፍሎቹ ውስጥ ሄዶ ማየት የተለመደ ተግባሪ ቢሆንም ነገር ግን በሕግ አይገደዱም። ቁልፎችን ከመመለስዎ በፊት የቤትዎን ሁኔታ በመዝገብ በጥንቃቄ መያዝዎን ያረጋግጡ። ተቀማጭ ገንዘብ ስለመመለስ ላይ ክርክር ከተነሳ እንኳን ፎቶ እና ቪዲዮ መያዝ አጋዥ ሊሆን ይችላል።

| | የመግቢያ ጊዜ ቅድመ ሁኔታዎች | የመውጫ ጊዜ ቅደመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|
| ምንጣፍ | ✓ ፍትሃዊ ሁኔታ - አንዳንድ የለቀቁ/ መስመሮች | ✓ ተመሳሳይ |
| መጋረጃ | ✓ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ | ✗ በድመት የተበላሹት |
| ጠረጴዛዎች | ✓ 1" የቃጠሎ ምልክት በ ዕቃ ማጠቢያ | ✓ ተመሳሳይ |
| ቀለም | ✓ አጠቃላይ ክፍሎቹን አዲስ መቀባት | ✗ ያልተፈቀደ ቀለም መቀባት በመኝታ ክፍል ውስጥ |

# የተቀማጭ ገንዘብ ተመላሽ መሆን

- የኪራይ ስምምነቱ በተጠናቀቀ በ21 ቀናት ውስጥ፣ የእርስዎ አከራይ ተቀማጭ ገንዘብዎን ለእርስዎ መስጠት አለበት ወይም ለምን የተወሰነው ተቀማጭ ገንዘብ እንደተያ በመግለጽ ሙሉ እና ግልጽ የሆነ መግለጫ መስጠት አለበት።
- የእርስዎ አከራይ 21 ቀናት ለሚጠይቀው ሕግ ተገዥ የማይሆን ከሆነ የስያትል (Seattle) የኪራይ የእርዳታ መስመርን ያግኙ።
- ስለጥፋት ከማልበስ እና ከመቅደድ ጋር፣ የጥገና ወጪዎችን እና ስላልተከፉ ዕዳዎች ክርክር ካልዎት በ Dispute Resolution Center of King County (ኪንግ ካውንቲ የክርክር መፍታት ማዕከል ማዕከል) መፈታት አለበት፤ *www.kcdrc.org* ወይም በትናንሽ ቅሬታ ማቅረቢያ ፍርድ በኩል፣ *www.kingcounty.gov/courts/district-court/small-claims.aspx* መፈታት አለበት።



# የአከራይ መብት

- የእርስዎ አከራይ መኖሪያ ቤቱን ለቀጣይ ተከራዮች፣ ሠራተኞች ወይም ገዢዎች ከ1 ቀን አስቀድሞ ማሳሰቢያ ለእርስዎ በመስጠት ለማሳየት መብት አለው።
- አስፈላጊ ወይም አስቀድሞ ስምምነት የተደረገበትን ጥገና ለማድረግ ከ2 ቀናት በፊት ማሳሰቢያ በመስጠት መብት ሊያገኝ ይችላል።
- አሳማኝ ምክንያት ካላችሁ ማለትም የቀጠሮ ግጭት ከተፈጠረ እንዳይገባ ሊከለክሉ ይችላሉ ነገር ግን አማራጭ ቀናት እና ጊዜያትን ማቅረባችሁን አረጋግጡ።
- ሁለታችሁንም ማለትም እርስዎን ወይም የእርስዎን አከራይን ክፍሉ ውስጥ ለመግባት አሳማኝ ምክንያት ሊኖራችሁ ይገባል።





# ማስወጣት

አከራይ Writ of Resolution (የተጻፈ ካሳ) ተከራይን ለማስወጣት ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ማምጣት አለበት።

ሂደቱም የማስገደድ ወይም የማስለቀቅ ማሳሰቢያን በመስጠት ይጀምራል።  ተከራዩ ቀነ ገደቡ ከመድረሱ በፊት ችግሩን መፍታት ካልቻለ፣ አከራይ 'ህጋዊ ያልሆነ መብት" በሚል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሲ ሊከፍት እና ተከራዩን የክስ መጥሪያ እና ቅሬታን ሊያመጣበት ይችላል። ተከራይ በተገለጸው ቀነ ገደብ ውስጥ ምላሽ መስጠት ወይም ሕግ ያለማክበር ፍርድ ላይ ሊወድቅ ይችላል። በመጨረሻ ላይ ዳኛውም ውጤቱን በ ጉዳይ ማያ ስሚ ላይ ይወስናል።

ከእርስዎ አከራይ ላይ ማሳሰቢያ ከተቀበሉ እና ከተቻለም መልቀቂን ለማስቀረት ከሞከሩ ወዲያውኑ ሕጋዊ ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ ነው። ከኪራይ መዝገብዎ ላይ መባረር ወደፊት ቤት መከራየትን ለእርስዎ አስቸጋሪ ሊያደርግ የሚችል ሲሆን የእርስዎንም ስም ሊያጠፋ ይችላል።

ለበለጠ መረጃ ወደ ስያትል (Seattle) የኪራይ አጋዥ መስመር ላይ ይደውሉ።


City of Seattle
Seattle.gov/rentinginseattle
የዕርዳታ መስመር (206) 684-5700



ስያትል (Seattle) በአሳታፊነት እና በእኩልነት ታምናለች። ስደተኞች እና በመጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ መምጣት ይችላሉ። የከተማ ሠራተኞች ስለ ዜግኔት ማንነት የማይጠይቅ ሲሆን የስደተኝነት ሁኔታ ላይ መሰረት ባለማድረግ ሁሉንም ነዋሪዎች ያገለግላል።

የአካል ጉዳት ካለብዎ እና በአማራጭ ፎርማት ከእኛ ላይ መረጃ ለመውሰድ ከፈለጉ፣ እባክዎን በአጋዥ መስመር ላይ ይደውሉልን። የTTY መስመራችን (206) 233-7156 ነው።

**የትርጉም አገልግሎት ሁልጊዜ ይሰጣል። ይህ ሰነድ የሚገኝበት በ፡**

English • Español • Oromiffa • af Soomaali • አማርኛ • ភាសាខ្មែរ • 中文 • 한국어 • ພາສາລາວ
русский язык • ภาษาไทย • ትግርኛ • Tiếng Việt